# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

## የኅዳር ወር አራተኛ ሰንበት

**በዚህ ዕለት ብርሃነ እውራን ተሰፋ ቅቡጻን መዋኤ ኃጌን አምላከ ብርሃን ስለመሆኑ እውራንን በሽተኞች ስለማዳኑ ይዘመራል።**

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ይቤሉ እስራኤል ኢርኢነ ወኢሰማእነ ዘእውሩ ተወልደ (እስራኤል እውር ሆኖ የተወለደ ሰው አሁን ቀደም አላየንም አልሰማንም አሉ)

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ፩ኛ ቆሮ ፪፤፩ - ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ዮሐ ፫፤፩-፯ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፫፤፴፬ - ፍጻሜ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ምስባክ

ደቂቀ ዕጓለ እመሕያው እስከ ማዕዜኑ ታከብዱ ልበክሙ
ለምን ታፈቅሩ ከንቶ ወተሐሱ ሐሰተ
አእምሩ ከመ ተሰብሐ እግዚአብሔር በጻድቁ

እናንተ የሰው ልጆች እስከ መቼ ድረስ ልባችሁን ታከብዳላችሁ
ከንቱ ነገርንስ ለምን ትወዳላችሁ ሐሰትንስ ለምን ትሻላችሁ
እግዚአብሔር በጻድቁ እንደተገለጠ (ተመሰገነ) እወቁ

መዝሙር ፬፥፪

**ወንጌል፥ ዮሐ ፱፤፩ - ፍጻሜ**
**ቅዳሴ፥ የጌታ ቅዳሴ (እግዚነ)**

## የዕለቱ ትምህርት

### «ጌታ ሆይ አምናለሁ» (ዮሐ ፱፤ ፴፰)

ማሳሰቢያ፥ የዕለቱ ወንጌል ቁልጭ ያለ ማብራሪያ የማያስፈልገው በመሆኑ ወይንም ከሚሰጠው ማብራሪያም በበለጠ የወንጌሉ ቃል (ዘሩ) ስለሚጠቅም አንባቢ ምዕራፉን በሙሉ በማስተዋል ቢመለከተው የበለጠ ይጠቅማል።

«ጌታ ሆይ አምናለሁ።» ይህንን ቃል የተናገረው ሰው አስቀድሞ የእግዚአብሔር ክብር ይገለጥበት ዘንድ እውር ሆኖ የተወለደ፤ ከጊዜ በኋላ የታወረ ሳይሆን እውር ሆኖ የተፈጠረ ሰው ነው (ቁ. ፩-፭)። መድኃኒታችን ይህንን ሰው ሲያይ በዓይን የሚታይ በሥጋ ላይ የሚፈጸም የተአምራት ሥራውን የማይሰራበት ዕለተ ሞቱን እያስታወሰ «በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ» ብሎ በምራቁ ያራሰውን ጭቃ ቀብቶ እንዲታጠብ አዝዞ ኣይኑን አበራለት (ቁ. ፮-፲፪)። ያም ቀን ሰንበት ነበርና ለማይረባ አእምሮ የተሰጡ የአይሁድ መምህራን «ይህ ሰው ሰንበትን አያከብርምና ከእግዚአብሔር አይደለም አሉ።» ይሁን እንጂ ኃጢአተኛ ሰው እንደነዚህ ያሉ ተአምራቶችን (ምልክቶችን) ሊያደርግ እንዴት ይችላል የሚሉ ባላእምሮዎች ሰዎችም አልታጡም (ቁ. ፲፫-፲፯)። መለያየት ሆነ። እውር የነበረውም ሲጠየቅ «ነቢይ ነው» ብሎ ተናገረ። አይሁድም የእግዚአብሔርን ማዳን ለመጠራጠር የሚያስችል ነገር ቢያጡ የእውሩን ሰው እውር ሆኖ መወለድ ተጠራጠሩና የእውሩን ወላጆች ፈልገው «እውር ሆኖ ተወለደ የምትሉት ልጃችሁ ይህ ነውን? ታዲያ እንዴት ያያል?» ብለው ጠየቁዋቸው። ኢየሱስን ክርስቶስ ብሎ የሚያምን ከምኩራባቸን ይሰደድ ብለው አይሁድ የወሰኑት ከንቱ ውሳኔ ያሰጋቸው ወላጆችም «ይህ ልጃችን እንደሆነ እውርም ሆኖ እንደተወለደ እናውቃለን። ዳሩ ግን አሁን እንዴት እንዳየ አናውቅም ወይም ዓይኖቹን ማን እንደከፈተ እኛ አናውቅም። ጠይቁት እርሱ ሙሉ ሰው ነው ስለራሱ ይናገራል።» ብለው የእግዚአብሔርን ተአምር ከመመስከር ዝም አሉ፤ ስለ ኢየሱስም ባለመናገር የምኩራብን ኑሮአቸውን አራዘሙ፤ ከፈሪሳውያንም ግልምጫ ተረፉ። ሃይማኖት እምቢ ያላቸው ፈሪሳውያንም ደግመው ጠርተው «እኛ ይህ ሰው ኃጢአተኛ እንደሆነ እናውቃለን» አሉት። ለእግዚአብሔር ክብር መግለጫ ሆኖ የተፈጠረው ሰው ግን «ኃጢአተኛ መሆኑን አላውቅም» አላቸው። እየደጋገሙ «እንዴት? በምን ዓይኖችህን ከፈተልህ?» እያሉ ቢዘበዝቡት «ደቀ መዛሙርቱ ለመሆን ትወዳላችሁን?» ብሎ ስለናደዳቸው «እኛስ የሙሴ ደቀ መዛሙርት ነን» ብለው እራሳቸውን ሲያከብሩ እርሱን ግን «አንተ የእርሱ ደቀ መዝሙር ሁን» ብለው ሰደቡት። አይገርምም? ወይ አለማወቅ?

ፈሪሳውያን በትንቢቱ ተጠቃሚዎች አይሆኑም እንጂ ትንቢት መናገር ይሳካላቸዋል። እንደ ሊቀ ካህናቱ ቀያፋ ጥሩ ትንቢት ተናግረዋል። የእነርሱንም ታላቅነት ከሙሴ አንጻር ሲገልጹ «ሙሴን እግዚአብሔር ተናገረው ይህን ሰው ግን ከወዴት እንደመጣ አናውቅም» አሉት። ለእግዚአብሔር ክብር የተፈጠረው ሰውም «ለወዴት እንደሆነ እናንተ አለማወቃችሁ ድንቅ ነገር ነው። ዳሩ ግን ዓይኖቼን ከፈተ። ከእግዚአብሔር ባይሆን ምንም ሊያደርግ ባልቻለም ነበር» ብሎ ክብሩን መሰከረ። ፈሪሳዊያኑ ግን «አንተ ሁለንተናህ በኃጢአት ተወልደህ አንተም እኛን ታስተምረናለህን?» ብለው ተናደው ከምኩራብ ውጭ በማይሰራው ስልጣናቸው ከምኩራብ አስወጡት። የእግዚአብሔርን ክብር የሚመሰክረው ከምኩራብና ከቤተ መቅደስ ተባረረ። ለራሳቸው ክብር የቆሙት ከምኩራብ ውስጥ ቀሩ። የምድራውያን መቅደስ በር ለተዘጋበት የሰማያዊው መቅደስ በር ተከፈተለት (ዮሐ ፪፤፲፱-፳፪)። እውነትና መንገድ የሆነ ጌታ ወደ ውጭ እንዳወጡት አውቆ ተቀበለው፤ መድኃኒታችንም «አንተ ሰው በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን?» አለው። እርሱም«… ጌታ ሆይ አምናለሁ» አለ። የክብር ጌታም «የማያዩ እንዲያዩ የሚያዩትም እንዲታወሩ እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ መጥቻለሁ» አለ። ክብር ለእርሱ ይሁን። ተመልካች ፈሪሳውያንም «እኛ እውሮች ነን» አሉት። «ኢየሱስም እውሮችስ ብትሆኑ ኃጢአት ባልሆነባችሁም ነበር (የሥጋ እውርነት ከመንግስተ ሰማይ አይወጣምና) አሁን ግን እናያለን ታላላችሁ፤ ኃጢአታችሁ ይኖራል» አላቸው።
ለብርሃነ እውራን ተሰፋ ቅቡጻን፣ ኃይለ ድኩማን ጌታ ክብር ይግባው።

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር … አሜን።**

ከመምህር ልዑለ ቃል አካሉ ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ ፩ኛ መጽሐፍ የተወሰደ …